# ደቀመዝሙር (39)

## ጥናት አንድ ማቴ 4፡12-22

የጥናት ዓላማ፡- የኢየሱስ ጥሪ ምንም እንኳን እርሱን በመከተል ይጀምር እንጂ በዚያ ላይ የሚያበቃ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን የእኛን ህይወት በመሥራትና በመቀየር ሌሎችን ሰዎች ወደ መንግሥቱ የምናጠምድ ሰራተኞች ማድረግንም የሚጨምር መሆኑን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…እሳ አጥማጆች ነበሩና መረባቸውን ወደ ባህሩ ይጥሉ ነበር። ኢየሱስም ኑ ተከተሉኝ ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ አላቸው። ወዲያው መረባቸውን ትተው ተከተሉት።›› ማቴ 4፡19

1. ማቴ 4፡12-22 በአንድነት ይነበብ። በቁ12-13 መሰረት፤ ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ መጥቶ ኑሮ ከመጀመሩ በፊት የት ነበረ? ኢየሱስ አገልግሎቱን በናዝሬት አካባቢ ከመቀጠል ይልቅ ወደ ገሊላ መጥቶ አገልግሎቱን የጀመረበት አንዱና ዋነኛ ሆኖ የምታየው ምክንያት ምንድነው?
2. ቁ12-17ትን ስናይ ዮሐንስ ትሁትና እንደ እርሱ ያለ ነብይ እንዳልተወለደ የተነገረለትን ሰው እግዚአብሄር ለምን ከህዝቡ ይወስዳል? መልካምና ታማኝ የነበረውን ዮሐንስን ላጡት ሰዎች እግዚአብሄር ኢየሱስን በመሰለ ከዮሐንስ በተሻለ አገልጋይ መባረኩ ለእኛ ምን ትምህርት ሊሆነን ይችል ይመስልሃል?
3. ኢየሱስ ናዝሬትን ጥሎ የመጣላትን ይህችን ከተማና በውስጧ የሚኖረውን ህዝብ ኢሳያስ በምን ዓይነት ሲገልጣት ነው የምናየው? በነብዩ አነጋገር የዚህች ከተማና የነዋሪዋ ህይወት የተቀየረው በምን ምክንያት ነው? በኢየሱስ ወደ ህይወትህ መምጣት ምክንያት በዚህች ከተማ ላይ የታየውን አይነት ለውጥ አምጥቷል ብለህ ታምናለህ ወይ?
4. በቁ17 ላይ ‹‹ከዚያን ጊዜ አንስቶ ኢየሱሰ…›› ሲል ጸሃፊው የትኛውን ጊዜ ሊጠቁመን ፈልጎ ነው? በቁ17 ላይ ኢየሱስ የሰበከውን ስብከትና፤ በማቴ 3፡1-2 ላይ ደግሞ ዮሐንስ ይሰብከው የነበረውን መልዕክት ጎን ለጎን በማየት፤ ጸሐፊው ‹‹ከዚያን ጊዜ አንስቶ ኢየሱስ…›› የሚለውን አነጋገሩን የበለጠ ለመረዳት እንድንችል ምን ፍንጭ ይሰጠናል ትላለህ?
5. በቁ18-20 ውስጥ ስለ ማንኛቸውንም ስለ ስምዖንና ስለ እንድርያስ የተነገሩትን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር።
6. ቁ21-22 ላይ ኢየሱስ ሲጠራ የምናየው እነማንን ነው? በቁ18-20 የተጠሩትን ሰዎችና በቁ21-22 የተጠሩትን ሰዎች ሁኔታ ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን በማነጻጸር ተናገር። የኢየሱስ ጥሪ ሲደርሰን ከእኛ ስለሚጠበቁት ነገሮች ይህ ክፍል ምን ፍንጭ ይሰጠናል ብለህ ታምናለህ?
7. ወደ ቁ19 ተመልሰን ስንመለከት፤ ኢየሱስም ‹‹ኑ ተከተሉኝ፣ ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ›› አላቸው። ከሚለው የኢየሱስ አነጋገር መነሻ ወይም መጀመሪያ መሆን ያለበት ነገር ምንድነው? እንደ መድረሻ አርጎ የተናገረው ነገርስ ምንድነው? በዚህ ሁሉ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ሚና ምን ትመለከታለህ?
8. በቁ19 ላይ ኢየሱስ ለሰዎቹ ባስተላለፈው ጥሪ ውስጥ የተካተቱ ሶስት ነገሮች አሉ ቢባል፤ እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው ? እነዚህ ሶስት ነገሮች በአንተ ህይወት ውስጥ እየተከናወኑ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? የኢየሱስ ደ ቀመዛሙርት እንደመሆናችን መጠን፤ እርሱን በመከተል የሚጀምረው ህይወታችን በኢየሱስ ተለውጦና ተሰርቶ ሰዎችን ለማጥመድ ደረጃ መድረስ እንደሚጠበቅብን ሰዎች ልንመላለስ ያስፈልገናል።

# <u>ጥናት ሁለት ዮሐ 6፡48-71</u>

የጥናት ዓላማ፡- ደቀ መዝሙር ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ህይወትም ከእርሱ በቀር በሌላ መንገድ ሊገኝ እንደማይችል የተረዳ ብቻ ሳይሆን፤ ከኢየሱስ በቀር ሌላ የሚያዛልቅና ተስፋ ሊሆን የሚችል እንደሌለ ተረድቶ የህይወት ዘመኑን ሁሉ ከእርሱ ጋራ ለመኖር የቆረጠ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ ጌታ ሆይ ወደማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ህይወት ቃል አለህ፤ አንተ አንድያ የእግዚአብሄር ቅዱስ እንደሆንህ አምነናል አውቀናልም፡፡›› ዮሐ 6፡68

1. ዮሐ 6፡48-71 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ48-51 ሲነበብ ተደጋግሞ የምናየው አንድ ቃል ምንድነው? በዚህ ክፍል ኢየሱስ ራሱን ሲያነጻጽር የሚታየው ከምን ጋራ ነው? በነዚህ ሁለት ዓይነት ምግቦች መሃል ጉልህ ሆኖ የምታያቸውን አንድ ተመሳሳይነትና አንድ ደግሞ ልዩነት ተናገር፡፡
2. ኢየሱስ በቁ53-58 ላይ ያለውን ሃሳብ እንዲናገር ያነሳሳው አንዱ ምክንያት ምንድነው? በቁ53-58 ያለው የክርስቶስን ሥጋ መብላትና ደሙን መጠጣት የሚለው ሃሳብ ቃል በቃል መወሰድ ያለበት ይመስልሃል ወይስ ኢየሱስ ምን ለማለት እንደፈለገ ነው የሚገባህ?
3. በቁ54-58 ውስጥ የኢየሱስን ሥጋ መብላትና ደሙን መጠጣት ስለሚያስገኘው ጥቅም የሚናገራቸውን ሁሉ በዝርዝር ተናገር፡፡ በቁ52 ላይ ተከታዮቹ ይከራከሩበት የነበረው ጥያቄያቸው ተመልሶላቸዋል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ አንተስ ሥጋውን የመብላትና ደሙን የመጠጣት በረከት ተካፋይ ለመሆንህ እርግጠኛ ሆነሃል ወይ?
4. ይከተሉት የነበሩት ደቀመዛሙርቱ በቁ60 ላይ ለምን ይመስልሃል ‹‹ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ ሊቀበለው ይችላል›› በማለት የተናገሩት?
5. ሥጋውን መብላትና ደሙን መጠጣት የሚለው አነጋገር በደቀመዛሙርቱ ውስጥ ማጉረምረምን እንደፈጠረ ኢየሱስ እንዴት ነው ሊያውቅ የቻለው? ይህ ሁኔታ ስለ ኢየሱስ የሚያስተምረን ወይም የሚያረጋግጥልን ነገር ምንድነው?
6. ቁ64 ላይ ኢየሱስ ‹‹ከእናንተ የማያምኑ አንዳንዶች አሉ፡፡›› በማለት የተናገራቸው ሰዎች እነማን ናቸው? አሳልፎ የሚሰጠው ወይም ይሁዳ ከዚህ ክፍል አነጋገር ስንመለከት ምድቡ ከምን ዓይነት ሰዎች ጋራ ነው? የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሆነው፣ እርሱን እየተከተሉና፣ እርሱን እያገለገሉ ያሉ ሰዎች ባላመኑ ሰዎች ምድብ ውስጥ መገኘት ምንድነው ሊያስተምረን የሚችለው?
7. ቁ67-71ን ስናነብ አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት እንዲመልሱት የተጠየቁት ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ከጴጥሮስ መልስ ስንረዳ ከኢየሱስ መለየት እንደማይፈልጉ የጠቀሳቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው?
8. አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት የጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስን ለብቻው ሊያስቀረው የሚችል ጥያቄ እንደነበረ እናውቃለን፡፡ ለምንድነው ታዲያ ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ ከመጠየቅ ወደኂላ ያላለው? ‹‹ጌታ ሆይ ወደማን እንሄዳለን›› ከሚለው የጴጥሮስ አነጋገር የምትረዳው ነገር ምንድነው? አንተስ ዛሬ ስለኢየሱስ የጴጥሮስ አይነት አመለካከት አዳብረሃል ወይ? ኢየሱስ የህይወት ቃል እንዳለው ማወቅና ማመን ብቻ ሳይሆን፤ ከእርሱ ሌላ መሄጃ እንደሌለ ተስፋ የሚሆን ስለሌለ ከእርሱ ጋራ ለመጣበቅ ልትወስን ያስፈልግሃል፡፡

<u>ጥናት ሶስት ማቴ 14፡22-36</u>

የጥናት ዓላማ፡- የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን የቆረጠ ሰው በእምነት እያደገ መሄዱ የግድ ስለሆነ፤ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጴጥሮስ ሄዶበት በማያውቀው መንገድና ተለማምዶት በማያውቀው ጎዳና ጭምር ኢየሱስ ሊያስኬደው ፈቃደኛ እንደሆነ መረዳት እንደሚኖርበት ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጴጥሮስም ከጀልባው ወርዶ  በውሃው ላይ እየተራመደ ወደ ኢየሱስ አመራ፡፡ ነገር ግን የነፋሱን ሃይል ባየጊዜ ፈራ፤ መስጠምም ሲጀምር ‹‹ጌታ ሆይ አድነኝ›› ብሎ ጮኸ፡፡›› ማቴ 14፡29-30

1. ማቴ 14፡22-36 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ22 ‹‹ወዲያውኑ›› ብሎ ከመጀመሩ በፊት የተከናወነውን ሃሳብ አጠር በማድረግ አንድ ሰው ይናገር፡፡ ዮሐ 6፡14-15ትን ስናነብ ይህ ኢየሱስ ያደረገው ተአምር ያስከተለው ነገር ምን ነበረ?
2. በቁ22-23 ላይ ኢየሱስ ህዝቡንና ደቀ መዛሙርቱን ካሰናበተ በኋላ በኋላ ያደረገው ነገር ምንድነው? በዮሐንስ 6 ላይ ካነበብከውና ሌሎቹንም በምንባቡ ውስጥ ያሉ ሁኔታዎች ሁሉ በማገናዘብ ስትመለከተው፤ የኢየሱስ ጸሎት በምን ላይ ያተኮረ ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ለምን ይህንን ልትል ቻልክ?
3. በቁ22 ላይ ስንመለከት ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ውስጥ ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት እንዳዘዛቸው እናውቃለን፤ በቁ24 ላይ ደግም ነፋስ ተነስቶ በማዕበል ሲንገላቱ እናያለን፤ ታዲያ ኢየሱስ በፈቀደውና እንዲያደርጉ ባዘዛቸው ነገር ውስጥ ነፋስና ማዕበል ሊያስቸግራቸው መቻሉ ለእኛ በምን መንገድ ትምህርት ሊሆነን ይችላል ትላለህ?
4. በቁ25-26 ላይ ሲሆን የምናየው ነገር ምንድነው? ለምን ይመስልሃል ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ክፍል ውስጥ እየሆነ ያለውን ነገር እንደ ምትሃት አድርገው የቆጠሩት?
5. በቁ22-26 ውስጥ በደቀ መዛሙርቱ ህይወት ውስጥ አስጨናቂ ሆነው የምናያቸው ሁለቱ ሁኔታዎች ምንና ምንድናቸው? በቁ27 ላይ የኢየሱስ ‹‹አይዟችሁ፤ እኔ ነኝ አትፍሩ›› የሚለው አነጋገሩ ለሁለቱም ሁኔታዎቻቸው መልስ የሚሆንላቸው በምን መንገድ ነው? ችግሮችህ ብዛት ቢኖራቸውም፤ ኢየሱስ ለሁሉም መልስ ሊሆን እንደሚችል ልብህ ተቀብሎታል ወይ?
6. ቁ28-30 በኢየሱስ በመሃላቸው መገኘት የጴጥሮስ ምላሽ ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት የሚለየው በምን ነበረ?
7. ማቴ 22-33 ውስጥ ያነበብነው ታሪክ በተለይም ለሁሉም ደቀ መዛሙርት የሚሆን አንድ ትልቅ ነገር ተምረዋል ብንል ይህ ትምህርት ምንድነው ትላለህ?
8. ኢየሱስ ጴጥሮስን በውሃው ላይ እንዲራመድ ‹‹ና›› ብሎ ሲጠራው ሊሰጥም እንደሚጀምር አስቀድሞ ያውቃል፡፡ ታዲያ ለምንድነው ሊሰጥም እንደሚጀምር አስቀድሞ እያወቀ በውሃ ላይ እንዲራመድ የጠራው? ተለማምደህ የማታውቀውን ነገር እንድታደርግ ኢየሱስ አዞህ ያውቃል ወይ? ደቀ መዝሙሩ እንድትሆን ሲጠራህ በእምነትህ እድገት እንዲታይ ስለሚጠብቅብህ አንዳንድ ጊዜ ተለማምደህ በማታውቀው ሁኔታ ውስጥ ሊያሳልፍህ ሊፈቅድ እንደሚችል ከጴጥሮስ ካለፈበት ህይወት መማር ትችላለህ፡፡

# <u>ጥናት አራት ማቴ 15፡1-20</u>

የጥናት ዓላማ፡- ጴጥሮስ ያልገባውን ጠይቆ ለመረዳት እንደሞከረ ሁሉ፤ ደቀ መዝሙርም ያልገባውን እንደገባው አድርጎ ሳያሳልፍ ዘወትር አዲስ እውነትን ለመማር፣ ለማወቅና ለመረዳት፤ ክፍት ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጴጥሮስም ምሳሌውን አስረዳን አለው፡፡›› ማቴ 15፡15

1. ማቴ 15፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዛሬው ምንባብ ውስጥ ተዋናኝ ሆነው የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ ዘርዝር፡፡ በቁ1-3 ላይ የፈሪሳውያኑ ጥያቄ ያተኮረው በምን ላይ ነበረ? ኢየሱስ የትኩረታቸውን አቅጣጫ ወደ ምን ሲያዞረው ነው የምንመለከተው? ዛሬስ ኢየሱስ እኛን ፊት ለፊት ቢያነጋግረን ከእግዚአብሄር ቃል ይልቅ ምን ያህል ህይወታችን በወግና በልምድ ይዘን በመጣነው ነገር ላይ የተመሰረተ ይሆን?
2. ቁ4 ‹‹እግዚአብሄር›› በማለት ሲጀምር ቁ5 ደግሞ ‹‹እናንተ ግን›› በማለት ይጀምራል፡፡ ከኢየሱስ አነጋገር እንደምንረዳው የእነዚህ ፈሪሳውያን ጥፋት ምን ነበረ? በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ለፈሪሳውያኑ ድርጊት በምሳሌነት ያቀረበው የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ምን የሚለው ነው? የእነርሱ ወግስ ይህንን አስመልክቶ ምን ይላል?
3. በቁ4-5 ውስጥ ‹‹አባትና እናትህን አክብር…›› እያለ ሲናገር ክብርን ከምን ጋራ ተገናኝቶ ነው የምንመለከተው? ከዚህ አንጻር ስንመለከተው በ1ኛ ጢሞ 5፡17 ላይ ስለ ሽማግሌዎች የሚናገረውን ጥቅስ በምን መልኩ ልንረዳው ብለህ ታስባለህ?
4. በቁ4-5 ላይ የኢየሱስን አነጋገር ስናነብ፤ ለምንድነው ሰው ለእግዚአብሄር የአምልኮ መባና መስዋዕት አድርጎ ከሚያቀርብ ይልቅ ለቤተሰቡ ማለትም ለወላጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ማሟላት የበለጠ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት እንደሚኖረው ያስተማራቸው?
5. በቁ7-9 መሰረት ኢሳይያስ ስለነዚህ ዓይነት ሰዎች ምን በማለት ነበረ የተናገረው? በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች የሰጣቸው ስም ምን የሚል ነው? ኢሳይያስ የተናገራቸው ንግግር አንተን የሚመለከትበት መንገድ ካለ ራስን መመርመር ክፋት የለውም፡፡
6. ቁ10-14 ላይ ኢየሱስ ህዝቡን ምን እንዲያደርጉ ነው ሲነግራቸው የምናየው? ህዝቡ እንዲያስተውሉ የፈለገው ነገር ምን ይመስልሃል? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የፈሪሳውያን መቆጣትና መናደድ ኢየሱስን ያላስገረመው ምክንያት ለምንድነው?
7. በቁ16-20 ላይ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የጠየቀው ምን በማለት ነበረ? እንደ ኢየሱስ አነጋገር ከሆነ፤ ከአፍ ከሚወጣውና ወደ አፍ ከሚገባው የበለጠ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው የትኛው ነው? ከአፍ የሚወጣው ሰውን እንደሚያረክስ ኢየሱስ የሰጠው ምክንያት ምንድነው? አንተስ ከአፍህ ለሚወጣው ነገር ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋለህ?
8. የደቀመዛሙርቱ አለማወቅ እንዲገለጥና ኢየሱስ የተናገረውን እውነት በግልጽ መረዳት እንዲችሉ አስተዋጽዖ ያደረገው ማን ነው? ጴጥሮስም እንደሌሎቹ ደቀመዛሙርት እንደገባው ሆኖ ዝምቢል ሊሆን የሚችለው ነገር ምን ነበር ብለህ ትገምታለህ? አንተስ የማታውቀውን እንደምታውቅ በማስመሰል የምትመላለስበት ጊዜ አለወይ? የጌታ ደቀመዝሙር ባለማወቁ ሳያፍር ጠይቆ የመማርና የመረዳትን ልምድ ማዳበር ትልቅ አዋቂነት እንደሆነ ሊረዳ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት አምስት ማቴ 18፡21-35

የጥናት ዓላማ፡- የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነ ሁሉ ከእግዚአብሄር እጅግ ብዙ ይቅርታን የተቀበለ እንደሆነ ተረድቶ፤ እርሱ ራሱም ለሚበድሉትና ለሚያሳዝኑት ይቅርታን ለመስጠት ዘወትር ፈቃደኛነትን የሚያሳይ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ ያደርግባችኋል፡፡›› ማቴ 18፡35

1. ማቴ 18፡21-35 በአንድነት ይነበብ፡፡ ‹‹በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ›› በማለት በቁ21 ላይ የተጀመረው ሃሳብ መነሻው ከየት እንደሆነ ተናገር፡፡ የጴጥሮስ ጥያቄ ‹‹ወንድሜ ቢበድለኝ›› ሲል በዳዩ ሌላ ሰው፤ ይቅር ባዩ ደግሞ ጴጥሮስ ነው፡፡ ይህንኑ ሃሳብ ጴጥሮስ ሌላ በምን መንገድ ሊጠየቅ ይችላል ነበረ ብለህ ታምናለህ?
2. ቁ21-22 ያለውን ክፍል ስናነብ ክርስትና ይቅርታን አስመልክቶ ከአይሁድ ሥርዓት የሚለይበትን ማወቅ ነው የፈለገው፤ ይቅርታ በሥርዓታቸው ከፍተኛው እስከ ሶስት ጊዜ ነው፡፡ ጴጥሮስ ሶስትን ከእጥፍ በላይ አድርጎ ሰባት ጊዜ ማለቱ ከኢየሱስ ምን ዓይነት ምላሽ የጠበቀ ይመስልሃል? ኢየሱስ ሰባ ጊዜ ሰባት ሲል እነ ጴጥሮስ ሁለቱን ቁጥሮች አባዝተው 490 ጊዜ ይቅር እንዲሉ ነው ወይስ ምን ሊያስተምራቸው ፈልጎ ነው?
3. በቁ23-25 ላይ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማይን በምንድነው የሚመስላት? በነዚህ ቁጥሮች ላይ ስናነብ አገልጋዩ ዕዳውን መክፈል ባለመቻሉ ሊደረግበት የታዘዘው ነገር ምን ነበረ?
4. ቁ26-27 ላይ ተበዳሪው ወይም ባለዕዳው ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? አንድ ታላንት ማለት ከ58-80 ፓውንድ ወርቅ ማለት እንደሆነ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ ይህ ሂሳብ ሲሰላ ሰውየው በብዙ ሚሌዮን የሚቆጠር እዳ እንደነበረበት እናያለን፡፡ ከብድሩ መጠን ጋራ ስናይ፣ ይህ አገልጋይ መክፈል የሚችልበት መንገድ ያለ ይመስልሃል ወይ? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ? ጌታው ስለባለ እዳው የተሰማው ስሜት ምን እንደነበረ ተናገር፡፡
5. ቁ28-30 ላይ ዲናር የሚለው በቀድሞ ሮማውያን የሚጠቀሙበት ሲሆን አንዱ ዲናር 16 ሳንቲም ነበረ፡፡ ሁለተኛው ባለዕዳ የነበረበት አጠቃላይ ብድር ስንት ነበረ? ከአበዳሪው ድርጊት የምትመለከተው ነገር ምንድነው? ሁለቱን ባለዕዳዎች ተመሳሳይነትም ሆነ ልዩነት በማነጻጸር ተናገር፡፡
6. ቁ31-34 ላይ ጌታው አገልጋዩን ምን በማለት ነው የሚጠራው? የመጀመሪያው አገልጋይ ሌላኛውን ጓደኛውን ይቅር እንዲለው ወይም እንዲምረው የሚገባበትን ምክንያት ጌታው ምን በማለት ነው ለአገልጋዩ የነቀፈው? ቁ26 ላይ ባሪያው እንዲታገሰው ሲለምነው ጌታው ሲቆጣ ሳይሆን ሲያዝን እናያለን፤ ጌታው ሲቆጣና ሲናደድ የሚታየው ምን ጊዜ ነው?
7. ኢየሱስ ምሳሌውን ሲያጠቃልል በቁ35 ላይ ምን ለማለት ነው የፈለገው? ቁ35ትንና ቁ21-22ትን ላይ ያሉትን ሃሳቦች በማጠቃለል በአንድ አረፍተ ነገር ለወገኖች ተናገር፡፡
8. የመጀመሪያው አገልጋይ የተበደረው ብድር ብዛትና እርሱ ያበደረው ብድር ሲነጻጸር ምን ይመስላል? የእነዚህ ሁለት ሰዎችን ታሪክ ለምንድነው አብዛኛውን ጊዜ ከእኛን ህይወት ጋራ ተመሳሳይነት አለው ለማለት የሚቻለው? ይቅርታ ማድረግ ምን ያህል ይቀልሃል? ደቀመዝሙር አንዱና ዋነኛው ከኢየሱስ ሊማር የሚገባው ነገር ብዙ ይቅር እንደተባለ ተረድቶ ይቅር ማለትን እንዲለማመድ ነው፡፡

# ጥናት ስድስት ሉቃስ 14፡25-35

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን ደህንነታችን አንዳች ያልከፈልንበትና ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነፃ ሥጦታ እንደሆነ ቢታወቅም፤ በአንጻሩ ኢየሱስ የሚጠብቅብን ዓይነት ደቀመዝሙር መሆን ግን፤ አለን የምንለውን ማናቸውንም ነገር ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንንም ጭምር የሚጠይቀን ውሳኔ መሆኑን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…እንዲሁም ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።›› ሉቃስ 14፡33

1. ሉቃስ 14፡25-35 በአንድነት ይነበብ። ኢየሱስ በዚህ ምንባብ ውስጥ እየተናገረ ያለው ለማን ነው? የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሊሆኑ የማይችሉ ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
2. በቁ26 ላይ እንደምናነበው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን ቤተሰቦቻችንን ሁሉና ራሳችንንም ሁሉ መጥላት እንደሚኖርብን ይነግረናል። በዚህ ቦታ ኢየሱስ ዘመዶቻችንንና ወዳጆቻችንን ሁሉ እንድንጠላ በማለት የተናገረው አነጋገር፤ ቀጥተኛ ትርጉም እንደሆነ ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋራ ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳይኖረንና ከእነርሱም ጋራ እንዳንቀራረብ ማለቱ እንደሆነ ነው ወይ የምትረዳው? አስረዳ።
3. ከኢየሱስ አነጋገር እንደምንረዳው ሕንጻን መስራት ወይም መገንባት ሲፈለግ አስቀድሞ መወሰድ የሚኖርበት እርምጃ ምንድነው? ይህንን ቅድመ ሁኔታ ሳይፈጽም ዝም ብሎ ህንጻውን መገንባት የሚጀምር ሰው ሊገጥመው ስለሚችለው ነገር ኢየሱስ ምን ይላል?
4. ቁ30 ላይ ‹‹…ማነጽ ጀምሮ ነበር፤ መደምደም ግን አቃተው።›› ሲል መጀመር መልካም ነገር አይደለም ማለቱ ነው ወይ? ይህንን ማለቱ ካልሆነ ታዲያ ምን ማለቱ ነው? የፈለገው? የሚከዚህ አንጻር የራስህን ክርስትና ህይወት አጀማመር ስትመለከተው ዘላቂነት እንደሚኖረው አድርገህ ነው ወይ የጀመርከው?
5. በቁ28-30 እና በቁ31-32 ላይ ያሉትን ሁለት ምሳሌዎች በደንብ በማጤን ይነበቡ። በእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ዋነኛ ሃሳቡን በሁለት ቃላት ብቻ ተናገር።
6. በቁ31-32 ላይ አስር ሺህ ሰራዊት ብቻ ያለው ንጉስ፤ ሃያ ሺህ ሰራዊት ያለውን ንጉስ መመከት አይችልም የሚለውን ሃሳብ ነው ወይ የሚያስተላልፍልን? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው?
7. ቁ34-35 ላይ ከሰፈረው ሃሳብ ስለጨው ባህርይ የተነገሩትን እውነቶች የምታየውን ያህል በመዘርዘር ተናገር። ‹‹ጨው መልካም ነው፤ ጨው መልካምነቱን ካጣ ግን…›› በማለት ኢየሱስ የተናገረው ንግግር ከደቀመዝሙርነት ህይወት ጋራ እንዴት ይገናኛል?
8. ደህንነትህ ምን ያህል አስከፍሎሃል? ዛሬ ባጠናነው ክፍል መነጽር ስትመለከተው፤ ደቀመዝሙርነት የሚያስከፍለው ነገር ምንድነው? የኢየሱስ ደቀመዝሙር እሆናለሁ ብለህ እርሱን ለመከተል ስትጀምር ምን ያህል እንደሚያስከፍልህ ገብቶህ ነበረ ወይ? ደህንነት ከጌታ የምንቀበለው ነጻ ስጦታ ሲሆን፤ ደቀመዝሙርነት ግን አሉኝ የምንላቸውን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም ሳይቀር የሚጠይቅ ውሳኔ እንደሆነ ልንረዳ ይገባናል።

# <u>ጥናት ሰባት ሉቃስ 10:1-20</u>

የጥናት ዓላማ፦ ከሁሉ በላይ ደስ ልንሰኝበትና ሊያስደንቀን የሚገባው ነገር እኛ ለእርሱ የሰራናቸው ድንቅና ተአምራቶች ሳይሆኑ እርሱ ለእኛና በእኛ ህይወት የሰራቸው ዘለዓለማዊ የሆኑ ነገሮች ሊሆን እንደሚገባው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ይሁን እንጂ መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚያ ደስ አይበላችሁ፤ ስማችሁ ግን በሰማይ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ።›› ሉቃስ 10፡20

1. ሉቃ 10፡1-20 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ‹‹ሌሎች›› የሚለውን ቃል ስንመለከት ጸሐፊው ሊነግረን የፈለገው ነገር ምንድነው? ስለ እነዚህ ሰዎች ተልዕኮ ከቁ1 ላይ ብቻ የምታያቸውን እውነቶች በመዘርዘር ተናገር። ሁለቱንም ጊዜ ሲልክ ሁለት ሁለት እያደረገ ነው (ማር 6፡6 ሉቃ10፡1)። ብዙ ቦታዎችና ወደብዙ ሰዎች መድረስ እንዲችሉ፤ አንድ አንድ እያደረገ ለየብቻ ያላካቸው ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ከዚህ ምን መማር እንችላለን ብለህ እንደምታምን ተናገር።
2. ቁ2-3ትን ስናይ በጊዜው ስለነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ለሰዎቹ ሲያስረዳ የነገራቸው ምን በማለት ነበረ? ጥቂት ሰራተኞች በማለት የተናገረው ስለማን ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ ስንመለከት መከሩን አስመልክቶ ጌታ የሱስ ክርስቶስ እነዚህ ሰባ ሁለት ሰዎች በምን መንገድ እንዲሳተፉ ነው የፈለገው? አንተስ በዚህ ውስጥ ሰራተኛ ነህ ወይስ ተመልካች?
3. ቁ3-7 ላይ እነዚህ ሰዎች የተሰጣቸው መመሪያዎች ምን የሚሉ ነበሩ? ‹‹ኮረጆ ወይም ከረጢት፣ ወይም ጫማ አትያዙ፤ በመንገድ ላይም ለማንም ሰላምታ አትስጡ›› የሚለውን መመሪያ ኢየሱስ ሲሰጣቸው ምን ለማለት ወይም ለማስተማር ያሰበ ይመስልሃል?
4. ተልዕኮውን የተቀበሉት ሰዎች በቁ8-12 መሰረት ዋነኛው ተልዕኮአቸው ምንድነው? መልዕክታቸውን ሰሚዎቹ ካልተቀበሏቸው ማድረግ የሚኖርባቸው ነገር ምንድነው? በቁ11 ላይ ‹‹ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት እንደቀረበች ይህንን እወቁ›› ሲል ጸሐፊው ለእንቢተኞቹ ሰሚዎች ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምን ይመስልሃል? ሰዎች አልሰሙንም ማለት የወንጌልን እውነት ይቀይረዋል ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል።
5. ቁ12-15 ኮራዚን፣ ቤተ ሳይዳና፣ ቅፍርናሆም የተባሉት ኢየሱስ በድንቅና በተአምራት ያገለገለባቸው ከተሞች ሲሆኑ፤ በዚህ ቦታ በብሉይ ኪዳን ከተፈረደባቸው ከሰዶም፣ ጢሮስና ሲዶና ጋራ ያነጻጽራል። ኢየሱስ ይህንን መናገሩ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
6. በቁ16 ላይ በመልዕክተኞቹ የሚነገረው ቃል ምን ዓይነት ሥፍራ ተሰጥቶት ነው የምናየው? ‹‹እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል...›› የሚለው አነጋገር ‹‹ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን›› ከሚለው በ2ኛ ቆሮ 5፡20 ላይ ካለው ሃሳብ ጋራ እንዴት ሊሄድ እንደሚችል አስረዳ። ቃላችን ይህንን ያህል ክብደት እንደሚሰጠው ስናውቅ መልዕክታችን ትክክለኛውን ወንጌል የሚያንጸባርቅ ሊሆን እንደሚገባው እንረዳለን።
7. ቁ17-19 ላይ ስንመለከት የተላኩት ሰዎች ሲመለሱ ለኢየሱስ ያበሰሩት ነገር ምን ነበረ? እነርሱ ይህንን ሪፖርት በነገሩት ሰዓት ኢየሱስ ደግሞ በመንፈሳዊው ዓለም ስለሚካሄደውና እርሱ ስላየው ነገር የነገራቸው ሃሳብ ምን የሚል ነው?
8. በቁ20 ላይ ኢየሱስ የተከታዮቹን አመለካከት ሲያርም እናያለን። የእርማቱ ዋነኛ ሃሳብ ምን ነበረ ትላለህ? የአንተንስ ልብ በደስታ የሚያፍለቀልቀው አንተ ለጌታ ያደረክለትና በእጅህ የሚከናወነው ድንቅና ተአምራት ወይስ እርሱ ለአንተ የሰራው ሥራ? በጌታ አገልግሎት ውስጥ በምናያቸው ድንቅ ነገሮች ደስታ ሊሰማን ቢችልም ዋነኛው የደስታችን ምንጭ ግን እርሱ የሰራልን ሥራ ሊሆን ይገባዋል።

# ጥናት ስምንት ዮሐ 21፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- ደቀ መዝሙር የሌሎችን የህይወት አቅጣጫና መጨረሻቸውን በመመርመር እድሜውን ሳይፈጅ፣ ጌታው ለእርሱ ለራሱ በሰጠው ጸጋና አገልግሎት ላይ ብቻ በማተኮር ኢየሱስ መከተልና ማገልገል እንደሚኖርበት ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ጴጥሮስም ባየው ጊዜ፣ ጌታ ሆይ እርሱስ? ብሎ ጠየቀ፡፡ ኢየሱስም እስክመለስ ድረስ በህይወት እንዲኖር ብፈልግ እንኳ አንተ ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተለኝ አለው፡፡›› ዮሐ 21፡21-22

1. ዮሐ 21፡1-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ላይ በመሪነት ደረጃ የምናየው ሰው ማን ነው? ይህ ሰው ስንት ተከታዮች ነበሩት? እነዚህ ሰዎች አሳ ማጥመድ ያደጉበት ስራ ሆኖ እያለ ሌሊቱን ሁሉ ምንም አሳ ሊይዙ አለመቻላቸው፣ በዮሐ 15፡5 ላይ ኢየሱስ ከተናገረው ነገር ጋራ በማነጻጸር ምን መማር ይችላሉ ትላለህ? አንተስ ለራስህ ከዚህ የምትማረው ትምህርት ምንድነው?
2. ቁ4-6 ደቀመዛሙርቱ ምንም አሳ እንደሌላቸው ሲነግሩት ኢየሱስ ያዘዛቸው ትዕዛዝ ምን ነበረ? ኢየሱስ መሆኑ እንዳላወቁ ክፍሉ ይነግረናል፣ ታዲያ ለምን ይመስልሃል የማያውቁት ሰው የነገራቸውን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኞች የሆኑት?
3. ቁ7-11 ላይ ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር ጌታ መሆኑን መረዳት ያወቀበት ምክንያት ምን ይመስልሃል? ቁ11 ላይ ‹‹ይህንን ያህል ቢያዝም መረቡ አልተቀደደም›› የሚለው አነጋገር በወንጌል ነፍሳትን ለምናጠምድ ሰዎች ምን መንፈሳዊ ትምህርት ሊኖረው እንደሚችል አስረዳ፡፡
4. ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ደቀመዛሙርቱ የነበሩበትን ሁኔታ በአንድ አረፍተ ነገር ተናገር፡፡ ቁ12-14 ሲደክሙና በከንቱ ሲለፉ ለነበሩት ደቀመዛሙርቱ የተናገራቸው አንድ ነግር ምን ነበረ? ከንግግሩ በኋላ ጌታ ያደረገው ድርጊት ምን እንደነበረ አስረዳ፡ ብዙ ሞክረው ላልተሳካላቸውና ለዛሉት ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ሲያደርግ ያየነው ነገር ለአንተስ ህይወት ምን ተስፋ ይሰጥሃል?
5. ቁ15-17 የኢየሱስ ጥያቄና የጴጥሮስ መልሶች በሙሉ በምን ላይ ያተኮሩ ነበሩ? ከጴጥሮስ መልስ በኋላ ኢየሱስ በማስከተል የተናገራቸው ነገሮችስ ትኩረታቸው ምን ነበረ? በአንተ አመለካከት በፍቅርና በሃላፊነት መሃል ያለው ግንኙነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ሃላፊነትህን የምትወጣው ከፍቅር ይሆን ወይስ ከግዴታ?
6. በቁ19 እና በፊሊ. 1፡20 መካከል ስላለው መመሳሰልና ሁለቱ ክፍሎች ሊያስተምሩን የሚችሉትን አንድ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
7. ቁ20-25ት ላይ ስናነብ ዮሐንስ ኢየሱስ እስከሚመጣ ድረስ አይሞትም የሚለው ወሬ የተነሳው እንዴት ነው? ሰዎች የተናገሩትን በትክክል ለመረዳት ጊዜ ሳይወስዱ ያልተጨበጠ ወሬን ማውራት በአካባቢህ ምን ያህል ችግር ነው ብለህ ታምናለህ? ለዚህ አይነቱ ችግርስ መፍትሄው ምንድነው ትላለህ?
8. ቁ20-22 ጴጥሮስ ከራሱ አልፎ በተጨማሪ ማወቅ የፈለገው ስለማን ነበረ? አንተስ ከራስህ ይልቅ የሰዎችን የህይወት አቅጣጫ ለማወቅ የሞከርክበት ጊዜ አለ ወይ? እግዚአብሄር ለራስህ ባቀደው ጎዳና ላይ መራመድ እንጂ የሌሎችን አገልግሎትና የኑሮ አቅጣጫ ለማወቅ ጊዜ ማጥፋት እንደማይኖርብህ ከኢየሱስ ተማር፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ማቴ 28፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- ለተልዕኮው ብቃት እንዳላቸው የማይመስሉት ደቀመዛሙርት ታዘው በእምነት እንደወጡ ሁሉ፤ እኛም በራሳችን ብቃት እንደሌለን ተረድተን፤ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ያለውን የኢየሱስን ከእኛ ጋራ መኖር በመታመን የተሰጠንን ተልዕኮ ለመፈጸም መውጣት እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንዲህም አላቸው፤ ወደ አለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።›› ማር 16፡15-16

1. ማቴ 28፡1-20 በአንድነት ይነበብ። ሁለቱ ማርያሞች ወደ መቃብሩ የሄዱበትን ወቅት አስመልክቶ ክፍሉ የሚናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ሴቶቹ ወደ መቃብር የሚያስኬዳቸው ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
2. የፈሩና የተንቀጠቀጡ ጠባቂዎቹ እዚያ እያሉ መልአኩ ለምንድነው ሴቶቹን እንዳይፈሩ ሲያበረታታቸው የምናየው? በቁ5-8 ስንመለከት መልአኩ ኢየሱስን አስመልክቶ ለሴቶቹ በማረጋገጥ የነገራቸው ነገር ምን ነበረ? ከዚህ የተነሳ እንዲያደርጉ የሰጣቸው ትዕዛዝስ ምን የሚል ነው?
3. ቁ8-10ን ስናይ በነዚህ ሁለት ሴቶች ላይ የተገለጹት ሁለት ዓይነት ስሜቶች ምንና ምንድናቸው? እነዚህ ሁለት ስሜቶች በነማርያም ላይ ሊታዩ የቻሉበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
4. መልአኩም ሆነ ኢየሱስ ሴቶቹን የላኩት ወደ አንድ አይነት ሰዎች ነው። መልአኩ ደቀመዛሙርት ብሎ ሲጠራቸው፤ ኢየሱስ ማን ይላቸዋል? ፈርተው የተደበቁትን፣ የካዱትን፣ መነሳቱን እንኳን ለማረጋገጥ ያልመጡትን ሰዎች በዚህ ዓይነት ስም መጥራቱ ምን ያስተምርሃል?
5. በቁ11-15 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ በራስህ አነጋገር አጠር በማድረግ ለወገኖች ተናገር። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከምናነበው ነገር ውስጥ የሰውን ልብ አስመልክቶ ምን የምትመለከተው አስገራሚ እውነት አለ?
6. ቁ16ና 17 ደቀመዛሙርቱ ባደረጉት ነገር ላይ ሲያተኩር ቁ18-20 ደግሞ ኢየሱስ ባደረገው ላይ ያተኩራል። ማቴዎስ ደቀመዛሙርቱ እንዳደረጉ የሚነግረን ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስናይ በደቀመዛሙርቱ መሃል ሌላ የተከሰተው ነገር ምን ነበረ?
7. ኢየሱስ በቁ 19 እና በቁ20 ላይ ኢየሱስ ወንድሞቼ ለሚላቸው ተልዕኮ ሲሰጣቸው እንመለከታለን። ደቀ መዛሙርቱ ተልዕኳቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸው በዚያን ሰዓት ከኢየሱስ ያገኙት ማረጋገጫ ምን ታያለህ?
8. ቁ17ትን ስናነብ ተልዕኮውን የተቀበሉት ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ? በማር 16፡14 የምናያቸውስ በምን ዓይነት ሁኔታ ያሉ ሰዎች ናቸው? ለወንጌል መልዕክተኛነት እንደማትበቃ የሚመስልህ ጊዜ አለ ወይ? ይህ በሰማይና በምድር ሥልጣን ያለው ኢየሱስ፤ ወንጌሉን ተሸክመን እንድንወጣ ሲያዘን ዘወትር ከእኛ ጋራ መሆኑንም ያረጋገጠልን ስለሆነ በእምነትና በእርሱ ሃይል ለመውጣት እንችላለን።